# የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራትን በተመለከተ

# ለድሬ-ገጽ የቀረበ ትምህርታዊ ፅሁፍ

በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት በጣም እያደገ በመምጣቱና የተማሪዎችም ቁጥር መጨመሩ የኑሮ ውድነትና የተፈላጊ ቁሳቁሶችም ዋጋ እየናረ በመሄዱ መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመድበው በጀት ከመጠን በላይ ከመሄዱም በላይ ተጨማሪ ዜጎችን በብዛትና በጥራት በተለያዩ የትምህርትና የሙያ መስኮች በመንግስት አቅም ብቻ ማሰልጠን /ማስተማር/ የማይቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱን በዚህ መስክ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

የሚኒስተሮች ም/ቤት ባወጣው ደንብ ቁጥር አንቀጽ 154/2000 እና አንቀጽ 4/5 መሰረት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወጪ መጋራት ማለት በፌደራል መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብተው የሚማሩ በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተጠቃሚዎችን መንግስት ለትምህርትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ የሚጋሩበት ስርዓት ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ሚዛናዊ በሆነ መልክ የከፍተኛ ትምህርትን በጥራት ለማዳረስ እና የመንግስት አቅም ለማጎልበት ለከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚዎች የመንግስትን ወጪ በተወሰነ መጠን እንዲጋሩ ማድረጉ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ለተግባራዊነቱ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 3/251/1995 እና ደንብ ቁጥር 325/1995 እንዲሁም የአፈፃፀም መመሪያ እንዲወጣለት ተደርጓል፡፡

# የወጪ መጋራት ዓላማዎችና ጥቅሞች

## የወጪ መጋራት ዓላዎች

የወጪ መጋራት ዋና ዋና ዓላማዎችና ጥቅሞች የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎን በፍጥነትና በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ፣ የከፍተኛ ትምህርትን ጥራት ማሳደግ፣ እያንዳንዱ ዜጋ የሀገሩን ሀብትና የራሱንም አቅም በማቀናጀት ኃላፊነትና ተቆርቋሪነት በሚሰማቸው መልኩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሀብትን በአግባቡ የመጠቀም ባህል እንዲዳብር ማድረግና ለከፍተኛ ትምህርት ከሚወጣው ወጪ አንፃር መንግስትን መርዳት ወይም ማገዝ ነው፡፡

## የወጪ መጋራት ጥቅሞች

የወጪ መጋራት ጥቅሞች ከጊዜ ወደጊዜ ብዙ ኢትዮጵያዊያን የከፍተኛ ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አሁን ያላቸውንና ወደፊትም ሊኖራቸው የሚችለውን የሰውና የማቴሪያል ሀብት በአግባቡ መጠቀም ያስችላቸዋል፡፡ የራሳቸውን ገቢ በመፍጠር ወጪያቸውን መደጎም ያስችላቸዋል፤ የከፍተኛ ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ለህብረተሰቡ ሊጠቅሙ የሚችሉባቸው የዕውቀት መስኮች እንዲዋቀሩ ይረዳል፡፡ ስለዚህ በወጪ መጋራት ስርዓት ውስጥ የሚያለፉ የከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎች በተቻለ መጠን በመረጡት የትምህርት ዘርፍ ፍላጎታቸውን

በመማር የተሻለ ዕድል ያገኛሉ። በዚህ ሁኔታ የሚሰለጥኑ ተማሪዎች የበለጠ ኃላፊነት የሚሰማቸውና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትንም የትምህርት አሰጣጥ የበለጠ ጥራትና ብቃት እንዲኖረው ያደርጋሉ። ትምህርትም ተወዳዳሪ ወደሆነው ገበያ እንዲገባ አስተዋፅኦ ስለሚያደርግና መንግስት ከወጪ መጋራት የሚገኘውን ገንዘብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን እንዲያጠናክርበት ያስችለዋል።

## የወጪ መጋራት ክፍያ እና አሰባሰብ

የክፍያ አሰባሰብ፣ ክትትል ቁጥጥርና አፈፃፀም ስርዓት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመድበው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን ለሚማሩባቸው ጊዜያት ለመኝታና ምግብ የሚወጣውን ወጪ ሙሉ ለሙሉ፣ ለትምህርት የሚወጣውን ወጪ ደግሞ 15% ከፍለው የሚማሩበት ስርዓት ተዘርግቷል።

## የደንቡ ተፈፃሚነት ወሰን

በደንቡ ቁጥር 154/2000 አንቀፅ 3 ላይ እንደተመለከተው የወጪ መጋራት ክፍያ የሚመለከታቸው ተማሪዎች ከ1996 የትምህርት ዘመን ጀምሮ ወደ ፌዴራል መንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የገቡ አዲስ ተማሪዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሁም የሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነባር ተማሪዎች ካሉበት ዓመት ጀምሮ ሲሆን በደንቡ አንቀጽ 4/5 መሰረትም ተማሪዎቹ ኢትዮጵያዊያን መሆን አለባቸው።

## የተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ

### መብት

ማንኛውም ተጠቃሚ በደንቡ አንቀጽ 5/1 በተመለከተው መሰረት በየዓመቱ የሚፈለግበትን የወጪ መጋራት ክፍያ ሙሉ በሙሉ በቅድሚያ ለተቋሙ ከከፈለ እስከ 5 በመቶ፤ በደንቡ አንቀጽ 5/2 መሰረትም ከምረቃ በኍላ በተመረቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚፈለግበትን ክፍያ ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ካጠናቀቀ እስከ 3 በመቶ ቅናሽ ያገኛል።

የስርዓቱ ተጠቃሚ ክፍያ ለመጀመር ከምረቃ ወይም ትምህርቱን ካቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ የአንድ ዓመት የእፎይታ ጊዜ የማግኘት መብት ያለው ሲሆን ተጠቃሚውም ስራ ሳይጀምር ከአንድ ዓመት በላይ ቢቆይ ስራ በጀመረ በ6 ወር ውስጥ ክፍያውን መጀመር አለበት። ይሁንና በአገራዊ ጥሪ ምክንያት ትምህርቱን ቢያቋርጥ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ የተማረበት ክፍያና ግዴታውን ሳያጓድል

ሲከፍል ቆይቶ ክፍያው ከመጠናቀቁ በፊት በጡረታ ቢገለል ወይም ቢሞት ቀሪው ገንዘብ ይሰረዝለታል፡፡

## ግዴታ

ማንኛውም ተጠቃሚ በደንቡ አንቀጽ 8 እና 4 መሰረት በመንግስት በተመረጡ መስኮች ለመሰልጠን ፈቃደኛ ከሆነ ክፍያውን የሚፈፅመው በአገልግሎት ስለሆነ ለሰለጠነበት ዓመት ቢያንስ ሶስት እጥፍ መንግስት በሚመድበው ቦታ ማገልገል አለበት ነገር ግን የተማረበትን የወጪ መጋራት ክፍያ አገልግሎት በመስጠት ለመክፈል ግዴታ ከገባ በኋላ ግዴታውን ሳይወጣ ውሉን ቢያፈርስ ያገለገለበት ዘመን ታስቦ ላላገለገለበት ዘመን የሚቀርበትን ክፍያ ከነወለዱ በአምስት ዓመት ውስጥ ከደመወዙ 1/3 እየተቀነሰ ክፍሎ እንዲያጠናቅቅ ይደረጋል፡፡ የሚፈለግበትን ክፍያ በሂደት በግብር መልክ በጥሬ ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የገባ ከሆነ በደንቡ አንቀጽ 6/1 መሰረት በየወሩ የደመወዙን 10 በመቶ መክፈል ይኖርበታል፡፡

የሚፈለግበትን ክፍያ ሳያጠናቅቅ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄድ ከሆነ በደንቡ አንቀጽ 6/7 እና በትምህርት ሚኒስቴር በወጣው የአፈፃፀም መመሪያ ተ.ቁ11 መሰረት በቅድሚያ መክፈል ወይም ላልተከፈለው የወጪ መጋራት ክፍያ ተተክቶ የሚከፈል ዋስ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በደንቡ አንቀፅ 7/1/ሀ/ መሰረትም ስለሚፈለግበት የክፍያ መጠን ከተማረበት ተቋም የመጠየቅና የተሰጠውን ማስረጃ ለቀጣሪው የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

በተጨማሪም በደንቡ አንቀፅ 8/1 መሰረት የሚሰራበትን ሙሉ አድራሻና በሌላ ቦታ ሰርቶ ከሆነ መረጃውን ለአሰሪው በመስጠት በአሰሪው አማካSነት ለፌዴራል ገቢ አገር ውስጥ ባለስልጣን ወይም ባለስልጣኑ ለሚወክላቸው የክልል መንግስታት ገቢ ሰብሳቢ አካላት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

# የአስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

በወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብ ደንቡን የማስፈፀም ኃላፊነት ያለባቸው የመንግስት አካላት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን እና የክልልና የከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ አካላት/በውክልና/ ሲሆን ተግባርና ኃላፊነታቸው

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የወጪ መጋራት ክፍያውን የተሰበሰበ ገቢ የሚደረግበትን የተለየ ሂሳብ ቁጥር መስጠት፣
- ትምህርት ሚኒስቴር ስለ ደንቡ አፈፃፀም መመሪያ ማውጣትና ስለወጪ መጋራት ስርዓት ለተጠቃሚውና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ በ3 ዓመቱ የወጪ መጋራት ክፍያና መከለስ እንዲሁም ከየትምህርት ተቋማቱ የሚተላለፉትን የተጠቃሚዎች ዝርዝር ከሚፈለግባቸው የዕዳ መጠን ጋር ለፌደራል ሀገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ማስተላለፍ ነው፡፡
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ተማሪው የሚጋራውን ወጪ ማስላትና በቅድሚያ ከፍለው መማር ከሚፈልጉት ተጠቃሚዎች ክፍያውን መሰብሰብ፣ ከምረቃ በኑላ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአገልግሎት መክፈል የሚፈልጉትን እንደየፍላጎታቸው ውል ማስፈረም፣ ተጠቃሚዎች ተቋሙን ሲለቁ ስለሚፈለግባቸው የወጪ መጋራት ክፍያ ጠቅላላ መጠን የሚገልጽ ማስረጃ መስጠት እና በየዓመቱ መጨረሻ በቅድሚያ ከፍለው በመማራቸው ከክፍያ ነፃ የሆኑትን በጥሬ ገንዘብና በአገልግሎት የሚከፍሉትን በመለየት ዝርዝራቸውን ለትምህርት ሚኒስቴር መላክ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ተቋሙን ሲለቁ ስለሚፈለግባቸው የወጪ መጋራት ክፍያ ጠቅላላ መጠን የሚገልፅ ማስረጃ ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ መስጠትና በየዓመቱ መጨረሻም በቅድሚያ ከፍለው በመማራቸው ከክፍያ ነፃ የሆኑትን በጥሬ ገንዘብና በአገልግሎት የሚከፍሉትን በመለየት ዝርዝራቸውን ለትምህርት ሚኒስቴር መላክ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን በበኩሉ በደንብ ቁጥር 91/95 አንቀጽ 11 ላይ እንደተመለከተው በርካታ ዝርዝር ተግባራት ያለው ሲሆን በጠቅላላው የወጪ መጋራት ክፍያን የመሰብሰብ የመከታተል፣ የመቆጣጠርና የማስፈፀም ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ለዚህም ተግባሩ አስፈላጊውን ስርዓትና አደረጃጀት በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ በየክልሉ ከሚቀጠሩና በግል ከሚሰሩ ተጠቃሚዎች የሚፈለገውን ክፍያ ከደመወዛቸውም ሆነ ከዓመታዊ ገቢያቸው እየተቀነሰ ለመንግስት ገቢ የሚሆንበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ የአሰሪ መ/ቤቶች/ቀጣሪዎች ግዴታስ
- በወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብ ተግባር ውስጥ በዋናነት ግዴታ የተጣለባቸው ተጠቃሚዎችን የሚያሰሩ የግልም ሆኑ የመንግስት ተቋማት ናቸው፡፡ በመሆኑም ተጠቃሚዎችን ቀጥረው የሚያሰሩ ቀጣሪዎች በደንቡ አንቀፅ 7 በተጣለባቸው ግዴታና የአቀናነስ ስርዓት መሰረት የወጪ መጋራት ክፍያውን ከተጠቃሚዎች ደሞዝ በየወሩ በመቀነስ የየወሩን የስራ ግብር ሲከፍሉ የወጪ መጋራት ክፍያውንም በአንድ ፔሮል ላይ በማሳየት አብረው በተለያየ ደረሰS መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ከደመወዙ ተቀናሽ መደረጉን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ለተቀጣሪው መስጠት አለባቸው፡፡ የተቀጣሪዎችን ዝርዝርም በሶስት ወር ውስጥ ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## የወጪ መጋራት ክፍያ በውክልና ስለመሰብሰብ

በአዋጅ ቁጥር 351/1995 እና በደንብ ቁጥር 154/2000 መሰረት የወጪ መጋራት ክፍያ የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጠው ለፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ሲሆን በክልሎች ውስጥ ከሚቀጠሩ ተጠቃሚዎች የሚሰበሰበው ክፍያ በተመለከተ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ የማመቻቸት ተግባር እንደሚያከናውን በደንቡ አንቀጽ 11/ሬ/ ላይ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የክልል መንግስታት ወይም ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚገኙ ማናቸውም መ/ቤቶች፣ ድርጅቶች አለም አቀፍና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው ከሚሰሩ ተጠቃሚዎች የሚሰበሰበውን የወጪ መጋራት ክፍያ የክልል መንግስታት የገቢ ሰብሳቢ አካላት በውክልና መሰብሰብ እንዳለባቸው በትምህርት ሚኒስቴር በወጣው የወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብ አፈፃፀም መመሪያ ተራቁጥር 13 ላይ ተመልክቷል፡፡

## የሌሎች ሰዎች ግዴታ

በመጨረሻም የወጪ መጋራት ክፍያ በግብር መልክ ከደሞዝ ተቀናሽ የተደረገ በየወሩና ከዓመታዊ ግብር ጋርም በየዓመቱ የሚከፈል በመሆኑና ያልተከፈለው ክፍያም የገቢ ግብር አዋጅ የሚፈፀምበት በመሆኑ ክፍያ አሰባሰቡንም ሆነ አፈፃፀሙን በተመለከተ ለሚከናወነው ተግባር ማናቸውም ሰው የግልም ሆነ የመንግስት ተቋም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/95 አንቀጽ 41 የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**ጥያቄ ወይም አስተያየት ካላችሁ በስልክ ቁጥሮቻችን**

**046-221-1684/046-220-4400 ደውለው ይጠይቁ**

**ዌብሳይት አድራሻ:- www.snnprsrevenue.gov.et**